# *Case Reports*

## Note

The following reports are cases decided by the Cassation Division of the Federal Supreme Court of Ethiopia. The purpose of publishing the cases is to make them known to the members of the legal profession. The case reports in a single issue of the *Journal* bring together interesting decisions on a give area of law. For this issue judgments on the subject matter of Family Law are chosen.

In selecting a particular judgment for publication the Editorial Committee do not want to imply that the judgment is definitive on any proposition or that it contains erroneous propositions. The cases are chosen for the interesting issue(s) of law they raise.

የሰበር መ/ቁ/ 23632
ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡** - ዓብዱልቃድር ሙሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡** - ወ/ት ፀዳለ ደምሴ -ቀረበች
**ተጠሪ**፡- አቶ ክፍሌ ደምሴ - አልቀረበም
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች የደቡብ ብ/ብሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ባቀረበችው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ወላጅ አባት ስለሆንኩ ፍ/ቤቱ ለሕፃኑ ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ይሾመኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ የሕፃኑን ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞታል፡፡ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን ከመወለዱ በስተቀር ምንም ዓይነት እርዳታ አላደረገም፤ ተንከባክቦም አላሳደገም በማለት የተቃወሞ አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ ሕፃኑ ከእናቱ የሚወርሰውን ሀብትና ንብረት ፍለጋ እንጂ ለሕፃኑ ጥቅም ብሎ ስላልሆነ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆን የተላለፈው ውሣኔ ተሽሮ በምትኩ እኔ አክስቱ ላለፉት 12 ዓመታት ተንከባክቤ ያሣደኩት ሞግዚት ሆኜ እንድሾም ይወስንልኝ በማለት ያቀረበችውን መቃወሚያ የወረዳው ፍ/ቤት መርምሮ አባት ላለው ልጅ አመልካች የሞግዚትነት ጥያቄ ማቅረብ አትችልም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን እስከዛሬ ድረስ ሣያሣድግ አሁን እናቱ ስትሞት ላሣድግ ማለቱ ሀብትና ንብረት ፍለጋ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚያዳግት ቢሆንም በደበቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 235/1 ከወላጆቹ አንዱ በሞት የተለየው ሕፃን በሕይወት ያለው ወላጅ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንደሚሆንለት ስለሚደነግግ የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጭን አስቀረቦ ሣያከራክር በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የለም በማለት የአሁኗን አማካች አቤቶታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር ቅሬታ ማመልከቻው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት መጋቢት 6 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በዚህ ጉዳይ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ አክስት የሆነችው የአሁኗ አመልካች ሞግዚት ለመሆን ያቀረበችውን ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ መልስ ሰጭም መጥሪያ ደርሶት መልሱን ባለማቅረቡ የጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር ቅሬታ ማመልከቻውን ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 ስለሕፃናት መብት ደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግሥታዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተቋማት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችና የአስተዳደር ባለሥልጣናት ወይም የሕግ አውጭው አካላት የሕፃናትን ደህንነት በቀደምትነት እንዲያስቡ በአስገዳጅነት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው የአለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል የሕፃናትን መብት በሚመለከት 1984 ዓ.ም. የፀደቀውና በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ የሕግ አካል የሆነው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) መሠረት ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች አካላት ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲሰጡ የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በዋነኛነት መመልከት እንደሚገባቸው ተመልክቷል፡፡ እንደሚታወቀው የልጆቻቸው መብትና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከወላጆቻቸው የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ሰው ሊኖር ስለማይችል ሕግ አውጭው በመርህ ደረጃ የተቀበለው በማሆኑ በሕይወት ያለው አባት ወይም እናት የሕፃን ልጁ ሞግዚት እና አስተዳዳሪ አድርጎ የመሾሙ አሠራር አገራችንን ጨምሮ የበርካታ አገራት ተሞክሮ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት በፌደራልም ሆነ በክልል የቤተሰብ ሕጎች ውስጥ ወላጆች ለሕፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ ስለመሆናቸው በግልጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ የተባለው ወላጅ በሕገ መንግሥቱ እንደተመለከተዉ ለሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት እስከሠሩ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደሆነ ሊስተዋል የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በአባት ወይም በእናት የሞግዚትነት ሽፋን የሕፃናትን መብትና ደህንነት የሚጎዱ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ ሥራዎች ሁሉ በዳኞች ቀሪ እና ፈራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ በሕጉ የተለያዩ ክፍሎች ማግኘቱ ይህንኑ የሕፃነን መብትና ጥቅም በዋነኛነት ለማስከበር የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉደዮችን ሲመረምሩ ከዝርዝር ሕጎቹ በተጨማሪ በሕገመንግሥት አንቀጽ 36(2) በአስገዳጅነት የተቀመጠውን የሕፃናትን ደህንነት ከግምት ወስጥ ያስገባ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የግል ይላል፡፡ ይህን በመተላለፍ የሚሰጡ ማናቸውም ውሳኔዎችና ለማዳዊ አመሠራሮች የሕገ መንግሥቱን ኃይለቃል የሚቃረኑ ስለሚሆኑ ፈራሽነታቸው የማያጠራጥር ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስናመራ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሕፃን ቢንያም ክፍሌን ሞግዚትነት አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲመረምሩ ከሕጎቹ ግልጽ ድንጋጌዎች ባሻገር ሕገመንግሥቱ ያስቀመጠውን የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም የማስከበር መርህ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው በተለይ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ደረጃ የሞግዚትነት ጥያቄ ያነሣው ሕፃኑ ልጅ "ከእናቱ በወርስ ከሚያገኘው ንብረትና ሀብት ላይ ተካፋይ ለመሆን አስቦ ስለመሆኑ" የከፍተኛው ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ ገልጾ ሕፃኒን ከመወለድ ወጭ

ከአስር ዓመታት በላይ ዞር ብሎ ያላየውን፣ ያልተንከባከበውን፣ ያላሣደገውን እንዲሁም ፍላጎቱን እንኳን ያልጠየቁትን ሕፃን በሰላምና በእንክብካቤ ካደገበት ቤት አስወጥቶ በአሁኑ ተጠሪ ሞግዚትነት ሥር ይተዳደር ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ያላገናዘበ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ከሕጎቹ ግልጽ ቃላት ባሻገር የሕጎቹን አላማና መንፈስ በቅጡ ሣያጤኑ የአንቀጾቹን ግርድፍ ቃላት ብቻ በመውሰድ ሕገመንግሥቱን በሚጋፋና የሕፃኑን መብትና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን የሰጡት የሞግዚትነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

**ውሣኔ**

- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ከፋ ዞን የቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 29/98 እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በየካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ. 01001 በተጨማሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ14275 የሰጡዋቸው ወልኔዎችና ትእዛዞች ተሽረዋል፤
- የአሁኗ አመልካች ወ/ሪት ፀዳለ ደምሴ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆና ሕፃኑ ከሟቹ ወላጅ እናቱ ከወ/ሮ ፋንታዬ ኃ/ሚካኤል የሚያገኘውን ማናቸውም የወርስ ሀብት ተረክቦ ሕፃኑን በሚልካም አስተዳደግና ደህንነት ተንከባክባ እንድታሣድገው ተሾማለች፡፡
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ/ 23021
ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ማንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
ተሻገር ገ/ሥላሴ
አብድራሂም አህመድ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህ - ጠበቃ አቸምየለህ ተፈሪ
**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የሟች አቶ አሚረ ይልማ ሚስት ናቸው ተብሎ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ተሽሮ ሚስት አይደሉም ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሆኑት ባቀረቡት አቤቶታ የሟች አቶ አሚረ ይልማ ሚስትነቴ ይረጋገጥልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ በሰኔ 24 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አመልካች የሟች አቶ አሚረ ይልማ ሚስት ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ከዚህ በኋላም የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም በሞግዚት አድራጊያቸው በወጣት ወንድወሰን አሚረ ስም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታወም ይዘት በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጌትነህና በሟች አቶ አሚረ ይልማ የነበረው ጋብቻ የቤተዘመድ ጉባኤ በሰጠው ውሣኔ እና ፍ/ቤቱም በሐምሌ 23 ቀን 1976 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ መፍረሱ የተረጋገጠ ስለሆነና አመልካቿም ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሟች ጋር በትዳር ያልኖሩ መሆናቸው ሟች ነዋሪ ከሆኑበት ቀበሌ ለባንክ በተፃፈ ደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ አመልካች ሚስት ሳይሆኑ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ሞግዚት የሆንኩለትን የወጣት ወንድወሰን አሚረን መብት የሚነካ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡

የተጠሪ መቃወሚያም ለአመልካች ደርሶ በሰጡት መልስ ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ ፈርሶ እንደነበር ሳይክዱ ከፍቺው በኋላ ንብረት ሳይከፋፈሉ ትዳራቸውን ቀጥለው እንደነበር ከፍቺው በኋላ በደንቡ መሠረት ጋብቻ አልተፈጸመም ቢባል እንኳ ጋብቻ መኖሩን በሁኔታ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የሚፈቅድ በመሆኑ ከፍቺ በኋላም እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን በምስክሮች ማስረዳት ስለሚቻል ከፍቺ በኋላ ጋብቻ አልተፈጸመም በማለት በተቃዋሚ የቀረበውን መቃወሚያ ወድቅ በማድረግ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲያፀናው በማለት ተከራክዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ በኩል የተቆጠሩትን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሟች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ በአመልካች ምስክሮች እንዳልተረጋገጠ በውሣኔው ላይ አስፍሮ ይልቁንም በአመልካች ልጅ በአቶ ዮናስ አሚረ ጥያቄ አመልካች ጋር የነበራቸው ትዳር በፍቺ ከፈረስ በኋላ እስከ እለተሞታቸው ትዳር እንዳልነበራቸው የሚያስገነዝብ ስለሆነ ጋብቻ

ስለሚጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ፍ/ቤቱ የሕግ ግምት ሊወስድ እንደሚችል በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 97/1/ ላይ የተደነገገ ሲሆን ይህ ግምት በበቂ ማስረጃ ሊፈርስ እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ 97/2/ ላይ ስለተመለከተና በአመልካችና በሟች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ በበቂ ማስረጃ የተስተባበለ ስለሆነ ቀደም ሲል አመልካች የሟች ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይና /አመልካች/ ሟች አሚረ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976 ዓ.ም. ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ለአራት ወራት ተለያይተው ኖረው መልስ ሰጪ ታርቀው እንደነበርና ጋብቻው ፈርሶ ከነበረ በኋላም የንብረት ክፍፍል ተደርጎ እንዳልነበረ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ አመልካችና ሟች መታረቃቸው ከተረጋገጠ የሚኖረወን ውጤት በተመለከተ የተፋቱ ባልና ሚስት ግንኙነታቸወን ለማደስ በፈልጉ እንደገና መጋባት አለባቸው ወይንስ በእርቅ ስምምነት ወደነበሩበት ይመለሳሉ የሚለወን የቤተሰብ ሕጉ ምላሽ እንደማይሰጥና ነገር ግን በሃገራችን ባሕል መሠረት የተፋቱ ባልና ሚስት ከፍቺ በኋላ ሲታረቁ ድጋሚ ጋብቻ ሲፈጽሙ እንደማይስተዋሉና የእርቅ ስምምነቱ በእራሱ እንደባልና ሚስት ለመኖር ሃሣብ ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በተመሳሳይም አመልካችና ሟች በፍቺ ከተለያዩ በኋላ መታረቃቸወን እንደ ባልና ሚስት ሆነው በጋብቻ የመኖር ውጤት ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ ከፍቺወም በኋላ ንብረት ያልተከፋፈሉ ስለሆነና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጋብቻ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

በዚሁ ውሣኔ ቅር የተሰኙትም የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታቸወን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የሟች ሚስት ነበርኩ የሚሉት አዲስ ጋብቻ ከሟች ጋር ፈጽመው ወይንም ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ታርቀን አብረን ኖረናል በማለት ስለሆነ መታረቅም ሆነ አብሮ መኖር ጋብቻን እንደሚጸም አያስቀጥርም የሚል ትችት አስፍሮ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር አመልካች የሟች ሚስት አይደሉም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ችሎቱ የቀረበወን አቤቱታ መርምሮ ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ወይንስ በሞት የሚለው ነጥብ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት እንደሚገባው በማለቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን በማዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የሕግ ነጥብ በአመልካችና በሟች አቶ አሜሪ ይልማ መካከል የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች እስከሞቱበት 1995 ዓ.ም. ድረስ በመካከላቸው በድጋሚ ጋብቻ ተፈጥሯል ወይንስ አልተፈጠረም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ የሕግ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካችና ሟች አቶ አሜሪ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976 ዓ.ም. ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ከአራት ወራት በኋላ ተመልሰው ታርቀው አብረው መኖር እንደጀመሩ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደርግ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 94 መሠረት ጋብቻ መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው በጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን የምስክር ወረቀቱ በሌለ ጊዜ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ጋብቻ እንዳለ ሚረጋገጥ እንደሚቻል በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 እና 97 ላይ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩልም የተፋቱ ባልና ሚስት በሚታረቁበት ጊዜ በድጋሚ ጋብቻ ሚፈጸም የሚገባቸው ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ በእርግጥ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በድጋሚ መጋባት አዲስ ጋብቻ ከመመሥረት የተለየ ስለማይሆን ድጋሚ ጋብቻ መመሥረትን በተመለከተ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ሊያስነሳ እንደሚችል ቢታመንም በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ሟች ከ10 ዓመት የጋብቻ ጊዜ በኋላ በ1976 ዓ.ም. ተፋተው ብዙም ሳይቆይ ከአራት ወራት በኋላ ሟች አስከሞቱበት 1995 ዓ.ም. ድረስ አብረው እንደኖሩ በአመልካች ምስክሮች የተነገረው ሲታይ እራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እንደሚቆጥሩና ኅብረተሰቡም ባልና ሚስት ናቸው በማለት የተቀበላቸው መሆኑን የሚያሳይና ይህም በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጋብቻ ሚፈጸሙ በአንቀጽ 97/1/ መሠረት የሕግ ግምት (Legal presumption) መወሰድ የሚቻል ሲሆን ይህንን የሕግ ግምት ማፍረስ የሚቻለው በአንቀጽ 97/2/ መሠረት ይህንን በሚያደው ወገን አስተማማኝ ማስረጃ በማቅርብ ጊዜ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካችና ሟች አቶ አሜሪ ይልማ ሲኖሩበት ከነበረው የቀበሌ አስተዳደር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተፃፈ ደብዳቤ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች ትዳር ያልነበራቸው መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ሕጉ እንደሚጠይቀው የሕግ ግምቱን ለማፍረስ አስተማማኝ ማስረጃ ሆኖ አልተገኘም፡

ውሣኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 21648 በታህሳስ 25 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32637 በሐምሌ 28 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጊታኀሁ በማቻ አቶ አሚረ ይልማ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩ ስለተረጋገጠ አመልካች የሟቹ ሚስት ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ/ 24625

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር ሙሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አማው

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የተመለከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

አቤቱታው የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ተከሣሽ የሟች ባለቤቴ ሙሑ ሰሌይማን ንብረት የሆነ ቤት ይዛ ስለምትገኝ የእኔንና ከሟች የወለደኩትን ልጄን ድርሻ ታካፍለን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽና ተከሳሽ የሟች ሚስቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱን ግማሽ ሁለቱ ይካፈሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለልጁ ይሁን በማለት ሲወስን፣ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተገዛው ሟች እና ተጠሪ ባፈሩት ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት በማስጠት አመልካች ከቤቱ ልትካፈል አይገባም ሲል ወስኖአል፡፡ የመጨረሻውን ይግባኝ የሰማው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት አመልካችና ሙሑ ሰሌይማን በጋብቻ ወስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ሆኖ ሳለ፣ አመልካችና ሙሑ ሰሌይማን አብረው አልኖሩም፣ ቤቱ የተገዛበት ሙሑ ሰሌይማን ከተጠሪ ጋር በነበረበት ጊዜ የተገኘ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከቤቱ ድርሻ የላትም የማለሉን አግባብነት መርምሮ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አከራካሪው ቤት የተሠራው በአመልካች እና በሟች ሙሑ ሰሌይማን መካከል ተመሥርቶ የነበረው ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ በተጋቢዎቹ መካከል የተመሠረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት የተገኘ ንብረት የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት

እንደሚወሰድበት በሕግ ተደንግጓል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ቀሪ ሚድረግ የሚቻለው አንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱ የግል ሀብቱ እንደሆነ ካስረዳ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አከራካሪው ቤት የሟቿ የግል ንብረት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ቤቱ የሟቿ የግል ንብረት መሆኑ በሕግ አግባብ ካልተረጋገጠ እና ከፍ ሲል የተጠቀሰወን የሕግ ግምት ቀሪ የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ አሜልካች በቤቱ ላይ መብት የላትም ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር አሜልካችን ከንብረቱ እንዳትካፈል ሚድረግ ደግሞ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሚፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለወን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሣኔ**

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07983 ታህሣሥ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05615 መጋቢት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአማራ ብ/ክ/መ/ የደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ሙሣኔ ፀንቶአል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዚሁ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ